# 30ኛው የኢትዮጵያውያን ባህልና ስፖርት ፌዴሬሽን ዝግጅት እንዴት አለፈ?

(ቴዲ - አትላንታ)

ከተመሰረተ 30 ዓመት ያስቆጠረው የባህልና ስፖርት ፌዴሬሽኑ ሠላሳኛ ዓመቱን ከጁን 29 እስከ ጁላይ 6 በሜሪላንድ ዋሽንግተን አክብሯል። በዚህ ዝግጅት ላይ ምን ያህል ሰው እንደተገኘ ከፌዴሬሽኑ በይፋ የተነገረ ነገር እስካሁን ባይኖርም ፣ ከ30ሺ ያላነሰ ሰው እንደነበር መገመት ግን ይቻላል። ስቴዲየሙ በጠቅላላ 54ሺ ሰው የሚይዝ ሲሆን፣ ቢያንስ ግማሽ ያሉ ቦታ ሞልቶ ታይቷል። በዚህ ውድድር በማሸነፍ ዋንጫ ለወሰደው የቨርጂኒያ ቡድን እንኳን ደስ አላችሁ እንላለን።

ይህ ዝግጅት በዓይነቱ ለየት ከሚልበት ነገሮች አንዱ የሆነውን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የማቀፍ ማዕከልነቱን ዘንድሮም አስከብሯል ማለት ይቻላል። ውድድሩም በደመቀ መልኩ ነው የተከፈተው። የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ተስፋዬ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልክት አስተላለፈዋል - ልዩ ልዩ የመክፈቻ ስነ ሥርዓትም ተከናውኗል። የደመቀ የመክፈቻ ዝግጅት ነበር ማለት ይቻላል።

ከዚያ ቀጥሎ ባሉት አራት ቀናት፣ ማለትም ከሰኞ እስከ ሃሙስ ድረስ በተለመደው መልክ የ30ዎቹ ክለቦች ውድድር በወጣለት ፕሮግራም ተከናውኗል። አንዳንድ ጊዜ የፕሮግራም መጋጨት አልነበረም ለማለት አይቻልም፣ ለምሳሌ የአትላንታ ቡድን ሶስተኛ ጨዋታውን ያደረገው፣ ባልተዘጋጀበትና ፎርፌ በልቻለሁ ብሎ በተዘናጋበት ሰአት እንደነበር የቡድኑ ተጫዋቾች ለአድማስ ሬዲዮ ተናግረዋል። በዚህ አጋጣሚ የአትላንታ ቡድን አንዴ እኩል ወጥቶ ፣ ሁለት ጊዜ ተሸንፎ ፣ ወደ ሁለተኛ ዲቪዚዮን ከመውረድ ለጥቂት ተርፎ መመለሱን መግለጽ ያስፈልጋል።

አርብ ጁላይ 5 ቀን የነበረው የኢትዮጵያ ቀን ዝግጅት፣ ለተወሰኑ ጊዜያት የመብራት መቋረጥ ከማጋጠሙና ያልተዘጋጁ የሚመስሉ አንዳንድ አርቲስቶች ከመቅረባቸው በቀር የተወጣለት ነበር። የሰአት መራዘሙ ግን በተለይ ልጆች ይዘው የመጡ ቤተሰቦች ሲንገላቱና የግድ አቋርጠው እንዲሄዱ ማድረጉ የታየ ነውና የሰአት ጉዳይ ሊታሰብበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል። እጅግ ደማቅ የሆነው ይህ የኢትዮጵያ ቀን ዝግጅት የሙዚቃ፣ የሙዚቃዊ ድራማ እና የክብር እንግዶች ንግግሮች የቀረቡበት ነበር። በዚህ ዝግጅት የሴቶች ጉዳይ ጎልቶ መነሳቱ ተገቢና ወቅታዊ ሆኖም አግኝተነዋል።

ከሰዉ ብዛትና ከሚታየው የአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ብዛት አንጻር ለጥቂት ጊዜ ኢትዮጵያ ያለን ቢመስል የሚደንቅ አልነበረም። ይህ ሁሉ ህዝብ ለአንድ ሳምንት በአንድ ቦታ ከተሞ የሚጋነን የጸጥታ ችግር ሳይገጥም ማለቁ ኢትዮጵያውያን ጨዋ መሆናችንን ያሳያል። ለዚህ ሁሉ ከአሜሪካ ግዛቶች ቀርቶ ከአውሮፓና ከኢትዮጵያ ጭምር በርካታ ተሳታፊዎች ለተገኘበት ዝግጅት ምክንያት የሆነው የሰሜን አሜሪካ ስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን በመሆኑ እንደ ተቋም ሊመሰገን ይገባዋል።

ይህም ሆኖ በፌዴሬሽኑ በኩል ችግሮች አልነበሩም ማለት አይቻልም፡ አንዳንዶቹ ጥቃቅን፣ ሌሎቹ የጎሎ ችግሮች ፣አንዱ ደግሞ በኛ እምነት ትልቅ ችግር ሆኖ ያገኘነውም ነበር። ምንም ፌዴሬሽኑ የኛ ቢሆን፣ ችግሩን እኛው ካልነገርነው ሌላ ሊነግረው አይችልምና አንዳንዶቹን ማንሳት ግድ ነው።

ገና ሲጀመር ፣ የክብር እንግዳ አመራረጥ ላይ ችኮላና የመወሰን ችግር እንደነበረበት ታይቷል። እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ በፌዴሬሽኑ ድረገጽም ሆነ በለቀቃቸው ማስታወቂያዎች "እንግዶቼ" ብሎ ከጠቀሳቸው ውስጥ ቢያንስ አራቱ ጭራሽ አልመጡም። የብሄራዊ ቡድናችን አሰልጣኝ አቶ ሰውነት ቢሻው፣ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ፣ መሰረት ደፋር እና ጢቂ ገላና ይመጣሉ ተብሎ የተነገረላቸው ግን ያልመጡ ናቸው። ለመሆኑ በርግጥ ግብዣውን ተቀብለዋል? ወይስ ደብዳቤ ስልተላከላቸው ብቻ ነው ይመጣሉ ተብሎ የተወሰነው? ወይስ እንመጣለን ብለው በኋላ ላይ ነው ሃሳባቸውን የቀየሩት? ይህን የሚመሉስት የፌደሬሽኑ ሃላፊዎች ይሆናሉ። 30 ዓመት እንደሞላው ትልቅ

ድርጅት ግን እንዲህ አይነት ስህተት መኖር አልነበረበትም። ከሆነም ደግሞ በግልጽ ምክንያቱን ለታዳሚው መንገርና ይቅርታ መጠየቅ ያስፈልግ ነበር።

ሌላው ችግር በምግብና ደረቅ ዕቃ ሻጮች ላይ የተፈጠረ ነው። እነዚህ ምግብና ደረቅ ዕቃ ሻጮች በያመቱ ገንዘብ ከፍለው ድንኳን በመከራየት ዝግጅቱን ከኪሱ ያላነሰ የሚያደምቁ ናቸው። ብዙዎቹ ብዙ ገንዘብ አውጥተው፣ በሳምንቱ ውስጥ ትርፍ ለማግኘት የተዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ነጋዴዎች ከሚያቀርቡት ቅሬታ አንዱ የመጀመሪያውን ሶስት ቀን መብራት ስላልተሰጣቸው ለሶስት ቀን ያህል ሥራቸውን አለመስራታቸውን ነው። ይህም ከተከፈለው 3200 ዶላር አንጻር የሶስት ቀን ኪሳራ አስከትሎባቸዋል። ምግብ አቅራቢዎቹ ይህንኑ ቅሬታቸውን በጽሁፍ ለፌዴሬሽኑ አሳውቀዋል፣ የሶስት ቀን ሂሳብ ተሰልቶ ማስተካከያ እንዲደረግም ጠይቀዋል። መልስ እየጠበቁም ይገኛሉ። የመኪና ማቆሚያም የነዚሁ የነጋዴዎች ሌላው ቅሬታ ነው። ለድንኳን ለከፈሉ ቢያንስ ለአንድ መኪና ነጻ ማቆሚያ መስጠት ሲገባው፣ ዕቃ ለመግዛትና ለማስገባት በወጡና በገቡ ቁጥር ለማቆሚያ 15 ብር በተደጋጋሚ መክፈል ነበረባቸው። ሌላው ቅሬታቸው ከፔፕሲ ምርት በቀር አታምጡ መባሉና እሱንም ራሱ ፌዴሬሽኑ ነበር የሚሸጥላቸው። ከውጭ ገዝተው ቢያመጡ የበለጠ እንደሚቀንስ ይናገራሉ።

የሙዚቃ ሲዲና ዲቪዲ ለመሸጥ የተመዘገቡት በበኩላቸው፣ ሲዲ ለመሸጥ የተመዘገቡት እነሱ ሆነው ሳለ፣ ሁሉም ባለድንኳን በትላልቅ ስፒከር ሙዚቃ መልቀቁና፣ አንዳንዶቹም ሲዲ ደርድረው ሲሸጡ እየታየ ያንን የሚቆጣጠር የፌዴሬሽኑ አካል አለመኖሩ በሥራቸው ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ይናገራሉ። ምግብ የሚሸጡትም፣ ፍላየር የሚያድሉትም፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶቹም ሁሉም እነዚያን የሚያካክሉ ስፒከሮች እንዲሰቅሉና ሙዚቃ ቤት እንዲመስሉ መፈቀድ አልነበረበትም ነው የሚሉት።

ለፌዴሬሽኑ ከፍተኛውን ክፍያ በመፈጸም (ጎልድ ስፖንሰር) የሆኑም ከችግሩ አላመለጡም። ያን ያህል ገንዘብ የከፈሉት እንደሚፈልጉትና እንደተስማሙበት ሊደረግላቸው ሆኖ ሳለ፣ ገንዘቡን እስኪከፍሉ የነበረው እንክብካቤ ገንዘብ ከከፈሉ በኋላ ድራሹ እንደጠፋ ነው የሚናገሩት። ከነዚሁ ድርጅቶች የአንዱ ተወካይ ሲናገሩ “ትልቁን ገንዘብ ከከፈሉት ውስጥ አንዱ ነን፣ ነገር ግን ድርጅታችንን በስፒከር እንኳን ለማስተዋወቅ፣ ሜዳው ድረስ ወርደን በተደጋጋሚ ማስታወስና መጨቅጨቅ ነበረብን” ይላሉ። ያም ብቻ አይደለም - የፌዴሬሽኑ ሃላፊዎች ርስ በርስ የሚነጋገሩ እስከማይመስል ድረስ አንዱ ያዘዘውን ሌላው አያውቀውም ይላሉ። በተያያዘም “በድንኳናችን ውስጥ ለሰዎች ስለ ሥራችን በርጋታ ማስረዳት የነበረብን ቢሆንም ከፊት ለፊታችን ያለው ድንኳን የተሰጣቸው ሰዎች ፣ ከሥራቸው በማይገናኝ ሁኔታ በትልቅ ስፒከር የሚለቁት ሙዚቃ እንኳን ለሰዎች ለማስረዳት ርስ በርሳችን እንኳን ማውራት እንዳያቅተን አድርጎናል ..” ይላሉ። የትኛው ድርጅት ከየትኛው አጠገብና ፊት ለፊት መሆን እንዳለበት እንኳን የተደረገ ጥናት አልታየም። እናም ትልቁን ክፍያ ፈጽመን፣ የፈለግነው ግን አልሆነም .... ይላሉ።

ከዚህ ቀደም በነበሩት [ለምሳሌ በአትላንታ] የስፖርት በዓል ወቅት የነጋዴዎች ድንኳን ቅዳሜ ጠዋት ተተክሎ፣ ሁሉም ከሰአት ዕቃውን አስገብቶ ለዕሁድ መክፈቻ ይዘጋጅ ነበር። በዘንድሮው የሜሪላንድ ዝግጅት ግን ድንኳን መተከል የጀመረው ቅዳሜ አመሻሹን ሲሆን፣ ዕጣ ወጥቶ ድንኳኑ ተከፋፍሎ ዕቃ ለማስገባት ጊዜው ባለመብቃቱ እሁድ መሸጥ በሚጀመርበት ቀን ገና ነጋዴዎች ዕቃ ለማስገባት ተገደው ነበር። ይህም ሌላው የነጋዴዎቹ ቅሬታ ነው።

የፌዴሬሽኑ አመራር አባላት ከውድድር በፊትና በውድድር ወቅት የተለያዩ ሰዎች መሆናቸው እንዳለፈው ዓመት ሁሉ ዘንድሮም ታይቷል። ከውድድር በፊት በቃለመጠይቆች የሚገቡት ቃል፣ በዚህ አንድ ሳምንት ውስጥ የት እንደሚገባ አይታወቅም። አንዱ ማስረጃ የመግቢያ ባጅን የሚመለከት ነው።

ፌዴሬሽኑ በአሰራሩ፣ ሁልጊዜም ቢሆን ለሚዲያ ሰራተኞች የሚዲያ ባጅ ይሰጣል - ወይም መስጠት አለበት። [ቢደላማ የጋዜጠኞች ማዕከል - [ሚዲያ ሴንተር] ሊዘጋጅም ይገባ ነበር] ... እናም ሁልጊዜ ከውድድሩ አንድ ወር በፊት ፎቶ ላኩ ይባላል፣ ዘንድሮም ፎቶ የላክነው ከወር በፊት ነው። ነገር ግን ማንም አስታውሶ መታወቂያውን ያዘጋጀ ሰው አልነበረም፣ ጭራሹኑ የተላከው ፎቶ ማን ጋር እንደደረሰ እንኳን ርስ በርስ መግባባት አልታየም። የመክፈቻው ዕለት የደረሱ ጥቂት ጋዜጠኞች በስንት ሙግት እዚያው እንደአዲስ ፎቶ ተነስተው መታወቂያ ሲሰጣቸው፣ በማግስቱና ከዚያ በኋላ የደረሱ በሙሉ የሚዲያ መታወቂያ የሚሰጣቸው አካል አልነበረም። ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የሚባሉት እንኳን አንዱ በአንዱ ከማሳበብ በቀር ምንም ሊፈይዱ አልቻሉም፣ የመግቢያው በር

ላይ የነበሩ አንዳንድ የፌዴሬሽኑ ሰራተኞች “ሚዲያ ከመለፍለፍ በቀር ምን ይጠቅማል? ተዋቸው ሲፈልጉ ከፍለው ይግቡ፣ ሳይፈልጉ ይመለሱ” ሲሉም ተደምጠዋል። በርካታ ጋዜጠኞች፣ ከሩቅ ከተማ ፎቶና ቪዲዮ ካሜራ ጭነው መጥተው በር ላይ ለክፍያ ከመሰለፋቸውና ከፍለው ከመግባታቸው በተጨማሪ ፣ እንደልባቸው ሰዎችን ለማነጋገርና ሜዳ ውስጥ ገብተው ለመዘገብ አልቻሉም። ለጋዜጠኞች መታወቂያ የሚሰጠው በር ላይ 20 ብር እንዳይከፍሉ ብቻ አይደለም፣ ቁምነገሩ መክፈሉም አልነበረም፣ ይልቁኑ ያለ ሚዲያ ባጅ በሁሉም ቦታ ተዘዋውሮ ለመስራትና ሰዎችን ለማነጋገር አለመቻሉ እንጂ! .. ነገር ግን ሁልጊዜም “ዘንድሮ ችግር የለም” እየተባለ ቀድሞ ይነገራል - ጊዜው ሲደርስ ግን ችግር አለ። የመግቢያ ባጅ ችግር የጋዜጠኞች ብቻም አይደለም። የፌዴሬሽኑ መስራቾችና አንጋፋ የቀድሞ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ጭምር፣ በፊት እንደሚደረግላቸው ዘንድሮ የመግቢያ ባጅ የሚሰጣቸው ጠፍቶ እየከፈሉ ሲገቡ ታይተዋል።

መኪና ማቆሚያ ቦታ ፊዴሬሽኑ ከሚተችበት ነገር አንዱ ሆኖ ተገኝቷል። በድረ ገጹ ላይ የተወሰነ ቦታ በነጻ የቀረው የጋራዥ ማቆሚያ ግን በ 5 ዶላር ማቆም እንደሚቻል ቢገልጽም፣ ሰዎች ሲገቡ ግን የተተከለው ማሽን ከ15 ዶላር በታች የሚቀበል አልነበረም። ለቅናሽ የሚሆን ኮድ ማሽኑ ቢጠይቅም ድረ ገጹ ላይ ግን የለም፣ ስለዚህ 5 ዶላር ብሎ የመጣ ሁሉ 15 ዶላር እየከፈለ ለማቆም ተገዷል። እንግዲህ በር ላይ የሚከፈልን አማካይ 20 ብር ጨምሮ አንድ ሰው ስቴዲየም ለመግባት ብቻ በቀን 35 ዶላር ያወጣል ማለት ነው።

በየቦታው ስለተደረጉት የመዝናኛ ዝግጅቶች ብዙ አቤቱታ አለ - በሌላ ዘገባ እንመለስበታለን። ነገር ግን ስለ መጨረሻው የቅዳሜ ማታ የመዝጊያ የሙዚቃ ዝግጅት ማንሳት ግዴታ ነው። ይህ የመጨረሻው ዝግጅት የሚደረገው በሰሜን አሜሪካ የስፖርትና ባህል ፌዴሬሽን ነው። ይህ ዝግጅት ፌዴሬሽኑ ጠቀም ያለ ገቢ ከሚያገኝበት ዝግጅት አንዱ እንደሆነም ይታወቃል። ለዚህ ነው በምሽቱ ሌላ ቦታ ሙዚቃ የማይኖረውና ፌዴሬሽኑ ብቻ የሚያዘጋጀው።

የዘንድሮው ዝግጅት የተደረገው በሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ ትንሿ ዝግ ስቴዲየም ነው። ይህ ዝግ ስቴዲየም በ1955 ዓም የተሰራ ሲሆን 15ሺ 450 ሰው ይይዛል። ታዲያ ፌዴሬሽኑ የሙዚቃ ዝግጅቱን እዚህ ስቴዲየም ሲያዘጋጅ ቢያንስ 10ሺ ሰው ቢመጣልኝ ብሎ መሆኑ አይጠረጠርም .. 3 እና 4ሺ ሰው ተጠብቆ ቢሆንማ ከስቴዲየም ይልቅ ትልቅ አዳራሽ ፌዴሬሽኑ ይከራይ ነበር ብለን እንገምታለን። የሚገርመው ግን ይህ ዝግ ስቴዲየም ጨርሶ አየር ማቀዝቀዣ የለውም። ፌዴሬሽኑም የተከራየው ማቀዝቀዣ እንደሌለው እያወቀ ነው።

ነገር ግን በጁላይ ወር የዲሲና አካባቢው ሙቀት፣ [ቀን ላይ በሜሪላንድ የሙቀቱ መጠን 101 ዲግሪ ደርሶ ነበር] የአየር ማቀዝቀዣ በሌለው ቦታ ዝግጅት ማድረግ ለምን ተፈለገ? በሙቀት የተነሳ ችግር ቢፈጠር ማን ነው ተጠያቂው? አንድ ሰው 40 ብር ከፍሎ ሲገባ ከሙዚቃው ባላነሰ የሚፈልገው ቢያንስ የማይሞቅና የማይቀዘቅዝ ቦታ ነው። አዳጊ ወጣቶች ነበሩ፣ ደካማ አዛውንቶች ነበሩ፣ ወጣቶች በላብ ተነክረዋል፣ ሴቶች ጸጉርና ልብሳቸው ተበላሽቷል። ሙዚቃውን ከሚያየው ያላነሰ ብዛት ያለው ሰው ውሃ ፍለጋ ወዲያ ውዲህ ሲል ነበር፣ በዚያ ዝግጅቱ በሚደረግበት ሌሊት እንኳን ወጥተን እንደለካነው ከሆነ የውጭው ሙቀት 82 ዲግሪ ነበር። በዚህ የሙቀት ወቅት፣ ማቀዝቀዣ በሌለው ቦታ ዝግጅቱን በማድረጉ ሊፈጠር ይችል ለነበረው ችግር ሃላፊነቱን ማን ነው የሚወስደው? የመጣው ሰው 2ሺ አካባቢ የሚገመት ሆነ እንጂ፣ እንደቦታው አያያዝ 10ሺ ሰው ቢመጣ ኖሮ ስንት ሰው በሙቀት መውደቅ፣ ስንቱም መታመምና ከዚያ በላይ ነገር ያጋጥም ነበር? ሆን ተብሎ አየር ማቀዝቀዣ እንደሌለው እየታወቀ ለሰው ጤንነትና ምቾት ምንም ሳይታሰብ ገና ለገና ብዙ ሰው ይይዛል ወይም ርካሽ ነው በሚል ምክንያት ከሆነ ፌዴሬሽኑ የተከራየው ተጠያቂነት አለበት። በዚህም በሙቀት የተሰቃየውን ታዳሚ ይቅርታ መጠየቅ፣ ድርጊቱን ሆን ብሎ የፈጸመው አካልም ሃላፊነት መውሰድ አለበት። የስቴዲየሙ ሃላፊዎች ይህንን ቦታ ላለፉት 10 ዓመታት ለንደዚህ ዓይነት ትልቅ ዝግጅት አከራይተውት አያውቁም። አንዱ ምክንያታቸው አየር ማቀዝቀዣም ሆነ ማሞቂያ ስለሌለው ነው። አሁንም አከራዮቹ እንደሚናገሩት ከሆነ በዚህ የፌዴሬሽኑ የማታ ዝግጅት ላይ ድንገት በሙቀት የተነሳ ችግር ቢፈጠር በሚል አምቡላንስ ደጅ እስከማቆም፣ ልዩ የማቀዝቀዣ ክፍልም ለብቻ አዘጋጅተው ነበር። ይህንንም ያደርጉት አከራዮቹ የዩኒቨርሲቲው ሃላፊዎች እንጂ ፌዴሬሽኑ አልነበረም።

የፌዴሬሽኑ በሆነው በዚህ የመጨረሻ ዝግጅትም 40 ዶላር ከፍሎ ለገባ ሰው አንዲት የክትፎ ሳንዱች 13 ዶላር፣ ቤቱ ማቀዝቀዣ እንደሌለውና በሙቀት የተቸገረው ሰዉ ወደደም ጠላም ሌሊቱን ሙሉ 4 እና 5 የሚጠጣው ውሃ እንደሚያስፈልገው እየታወቀ አንድ ውሃ 3 ዶላር መሸጥ ተገቢ ነው? ይህ እሳት ለኩሶ፣ በጎን እሳት ማጥፊያ ለገበያ እንደማቅረብ አይቆጠርም? ለመሆኑስ ምግብና መጠጥ በዚህ ዋጋ እንዲሸጡ የተፈቀደላቸው ነጋዴ ከሌሎች

ጋር በግልጽ ተወዳድረው ያገኙት ቦታ ነው? ሁልጊዜ ይደረግ እንደነበረው ለምን ሌሎች ቀን ስቴዲየም በጸሃይ ሲራወጡ የነበሩ ምግብ ሻጮችም በጨረታው እንዲወዳደሩ ክፍት አልተደረገም?

በመጨረሻ፣ የሚቀጥለውን ዓመት ውድድር ፌዴሬሽኑ እዚያው ሜሪላንድ ሊደግመው አስቧል የሚሉ ጭምጭምታዎች ይሰማሉ። ካልሆነ እሰየው፣ ከሆነ ግን ይህ በራሱ ሌላ ክርክር የሚያስነሳ ከመሆኑም በቀር "ኢትዮጵያውያንን አንድ ማድረግ" የሚለውን የፌዴሬሽኑን አቋም የሚጻረር ነው። ኢትዮጵያውያን አንድ የሚሆኑት እኮ ተመሳሳይ ከተማ ስለተሰባሰቡ ብቻ አይደለም፣ አንዴ አንዱ ጋር፣ ሌላ ጊዜ ሌላው ከተማ እየሄዱ ስለሚቀላቀሉም እንጂ። እንዲህ ዓይነት ትልቅ ውድድር ሲያልቅ ሁሉም ሰው እንደ ሰበር ዜና የሚጠባበቀው ጉዳይ "በሚቀጥለው ዓመት የት ይሆን?" የሚለውን ጥያቄ ነው ..፣ አሜሪካንን ለሁለት ከፍሎ ምስራቅና ምዕራብ እያፈራረቁ የሚደረገውን የውድድር ባህልም የሚያፈርስ ነው ...፣ ሌሎች ከተሞች ያሉ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ይህን ውድድር እየጠበቁ በመስራት ከኪሳራ ድነዋል፣ አዳዲሶች ተከፍተዋል ..፣ አዳዲስ ሥራ ተፈጥሯል .. ሰዎች ..አዳዲስ ከተማ በያመቱ እያዩ ለኑሮ የሚመችን በመምረጥ ወደዚያ ከተማ ኑሯቸውን ቀይረዋል፣ ...፣ ይህንን የፌዴሬሽናችንን የዓመት ውድድር እየጠበቁ ዘንድሮ ደግሞ ባጋጣሚው ያላየነውን ግዛት ልናይ ነው እያሉ ልምድ ያደረጉ ብዙ ናቸው ..፣ ... እርግጥ ነው ሜሪላንድና አካባቢው ቢሆን ፌዴሬሽኑ ብዙ ገንዘብ ሊያገኝ ይችል ይሆናል። ግን የታየው "የሚገኘው ገንዘብ ብቻ ከሆነ" የንግድ ድርጅት ሆኗል ማለት ነው። ከሆነ እሱን ተቀብለን ጸጥ እንበል። ዴንቨርም ያሉ፣ ሲያትልም ያሉ፣ አትላንታም ያሉ፣ ካሊፎርኒያም ያሉ .. ወዘተ. የኛ ዝግጅት የሚሉት አንድ ቀን ከተማቸው ውስጥ እንደሚደረግ ስለሚያውቁም ጭምር ነው። በተደጋጋሚ ዲሲ ብቻ እናዘጋጃለን ያሉ ሌሎች እኮ "የዲሲ ዝግጅት" እየሆኑ እንደመጡ የሚታይ ነው። ፌዴሬሽናችን የ30 ዓመት ከተማን ከከተማ ፣ ኢትዮጵያዊን ከኢትዮጵያዊ በየከተማው እያዞረ የማገናኘት ባህሉ በማይሆን ውሳኔ እንዳይጠፋ ሊታሰብበት ይገባል።

30 ዓመት የቆየና ኢትዮጵያውያን በአንድነት የሚገናኙበት ብቸኛ ድርጅት በግለሰቦች ምክንያት መልካም ስሙን ማጣት የለበትም። ሥራቸውን በአግባቡ የማይሰሩ ግለሰቦች ሊቀየሩ ይችላሉ። ፌዴሬሽኑ ግን ለዘላለም ይኖራል።

(የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አቶ ቴዎድሮስ በአትላንታ ከተማ የአድማስ ሬዲዮ አዘጋጅ ናቸው)